# ለዴሞክራሲያዊ ለዉጥ የጋራ ትግል
## ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት ድጋፍ ኮሚቴ በሆላንድ

ዛሬ በዴልፍት ከተማ የ2007 ዓ.ምን የእግር ኳስ ዉድድር ለመሳተፍ ከአዉሮፓ አሕጉር የተሰበሰባችሁ የእግር ኳስ ተጫዋቾች፣ ስፖርተኞችና ደጋፊ ዜጎች!!!

በሆላንድ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት የድጋፍ ኮሚቴ እንኳን ደሕና መጣችሁ እያለ ልባዊ ሰላምታዉን ያቀርብላችኋል ።

የቅንጅት መሪዎችና የተወሰኑ የነፃ ጋዜጤኞች አባላት ከአንድ ዓመት ተኩል እንግልት በሁዋላ ከኢሕአዴግ እስር ቤት በመፈታቸዉ፣የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች፣ የኢትዮጵያን አንድነትና ልዑላዊነት ለማስከበር የተስለፉችሁ፣ ለዴሞክራሲአዊ ለዉጥ መስወትነትን የከፍላችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ።

በምርጫ 97 የተሸነፈዉ አሸባሪዉና አምባገነኑ ስርዓት የቅንጅትን መሪዎችንና የተወስኑ የነፃ ጋዜጣ አዘጋጆችን በመፍታቱ በምርጫዉ ማግስት ለፈጸማቸዉ የአፈናና የግድያ ወንጀሎች ከተጠያቂነት እንዳይሸሽግ ድምፁን የተነጠቀዉ የኢትዮጵያ ሕዝብና የተቃዋሚዉ ሓይሎች ለሚያደርጉት ዘመቻ የዜግነት ግዴታችንን ያለማወላወል በጋራ እንድንወጣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት ጥሪዉን ያደርጋል።

በመሆኑም የወሳኙ ትግል አቅጣጫ፣

1- ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ዕዉን የሚሆነዉ በነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንጂ ገዢዉ ድርጅት በዴሞክራሲ ጎዳና የተከልኩአቸዉን ዉስብስብ መሰናክሎችን አልፋችሁ ስልጣን ተጋሩኝ፣ በኢሕአዴግ ማዕከልነት ለሚረጋገጥ ስልጣንም ተወዳደሩኝ እያለ ተቃዋሚወቹን የሚያስገድድበትን የአፈናና የማስፈራሪያ ስልቱን ለአንዴና ለመጨረሻዉ ለማምከን

2-ከዚህ በፊት በተደረጉ ምርጫ ተብዬ ማጭበረበሪያዎችም ሆነ በምርጫ 97’ የተነጠቀዉን የሕዝብ ድምፅ ለስልጣን ባለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲመልስ በተባበረ ሓይል ለማስገደድ፤

3-በተቃዋሚዎች መካከል የሚነሱትን ልዩነቶችን የሚመረምርና የመፍትሔ ሐሳብም የሚያቀርብ ሕዝብንና አገርን ያስቀደመ መፈትሔ የሚያፈላልግ የጋራ ኮሚቴ ለመሰየም፤

4-ባዕዳን ሓይሎች ለራሳቸዉ ጥቅም ሲሉ ወያኔ / ኢሕአዴግን በርታ አይዞህ! ማለታቸዉን እንዲያቆሙና ከወያኔ ስርዓት በሁዋላም ለሌላ በታኝና ከፋፋይ ሓይል አሳልፈዉ ለመስጠት በዝግጅት ላይ መሆናቸዉን አዉቀን በተባበረና ተከታታይ በሆነ የዲፒሎማሲ ዘመቻ ለአፋኙ ስርዓት የሚለግሱትን ሁለገብ ርዳታ ለማሰቆም፣

5-የተቃዋሚ ሓይሎች ያነገቡአቸዉ ጥያቄዎችና የፖለትካ መርሐግብሮች ምላሽ እስኪያገኙ ድረስ የጋራ ትግል ወሳኝነት የሚመነጨዉ ባገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት፣ ይህንን አስከፊና አደገኛ ሁኔታን በመገምገም፣ የጋራም መፍትሔ ማፈ ለግ አማራጭ የሌለዉና የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ነዉ ብሎ በማመን ሁሉን አቀፍ የጋራ ጉባዔ በሁሉ ሰላም ወዳድ ሓይሎች ትብብር እንዲጠራ ያላሰለሰ ጥሪ በማቅረብ ላይ ይገኛል። ከትብብር ዉጪ በምን መንገድ ይችን አገር ማዳን እንደማይቻል በመገንዘብ፤ የተደራጁም ሆኑ ያልተደራጁ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን በጋራ ሆነዉ አገር አድን ዕቅድ የሚነድፉበት የጋራ ጉባዔ በጋራ እንዲጠራ ባክብሮት እንጠይቀለን።

ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ !!!
የተሰረቀዉ የህዝብ ድምፅ ይመለስ !!!

July 29, 2007